*ዮሐንስ አ.*

# ለኤርትራ ችግር መፍትሔ የሥርአት ወይስ የሰው ለውጥ?

ኤርትራ እንደ ሉአላዊት አገር እውቅና ተሰጥቷት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከተመዘገበች ከ 20 ዓመታት በላይ ዕድሜ አስቆጥራለች፡፡ በወቅቱ የደርግን ስርዓት በመገርሰስ ኢትዮጵያን በመምራት ላይ የነበረው ኢህአዴግ የኤርትራ ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ብቻ መፈታት አለበት የሚል ጽኑ አቋም የነበረው በመሆኑ፣ የኤርትራ የነጻነት ጥያቄን አንግቦ ሲዋጋ በነበረው ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ የአሁኑ ህዝባዊ ግንባር ለዴሞክራሲና ፍትህ (ህግደፍ) ዘንድ ‹ቅኝ ገዢ› ተብላ ተፈርጃ በነበረችው ኢትዮጵያ የነጻነት ግንባሩን ጥያቄ ሊያስተናግድ የሚችል አንቀጽ በህገ መንግስት በማስፈር የሁለቱን አካላት ፍቺ ሰላማዊ እንዲሆን በመደረጉ እንደዚሁም አብዛኛው ሊባል የሚችል የኤርትራ ህዝብ የነጻነት ጥያቄውን መደገፉና ይህንንም ለሪፈረንደም በተደረገው ምርጫ 99% የሚሆነው ህዝብ የኤርትራን ነጻነት የደገፈ በመሆኑ ባጠቃላይ የ Decolonization ሂደቱ ከምንም ጊዜ በላይ ሰላማዊ የነበረ በመሆኑ ኤርትራውያን አገራቸውን ለመገንባትና ለማሳደግ ወርቃማ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል የሚል እምነት የአብዛኞቹ የፖለቲካ ተንታኞች እምነት ነበር፡፡

በርግጥም የኤርትራ ህዝብ ከነበረው አገራዊ ስሜት እና የነጻነት ግንባሩ ካሳለፋቸው አሰልቺ የሽምቅ ውጊያ ዓመታት አንጻር ሲመዘን በስልጣን ላይ ያለው ቡድን እንደዚህ አይነት ምቹ ሁኔታ ሲያገኝ አገር ለማበልጸግና የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ይተጋል  እንጂ ከህዝቡና ከአገሪቱ ፍላጎት በተቃራኒ ይጓዛል የሚል ግምት ለመያዝ አዳጋች ነበር፡፡

ይሁንና ከአብዛኛው ኤርትራዊና የፖለቲካ ተንታኞች ግምት ውጪ በተለይ በፕሬዚዳንት ኢሳያስና በቡድናቸው አባባል ያቺ የምስራቅ አፍሪካ ታይዋን/ሲንጋፖር ትሆናለች የተባለች አገር በሚያስገርም ሁኔታ ሁሉንም ጎረቤቶችዋ የተነኮሰች እና ከሁሉም ጎረቤቶችዋ ጋር ጦርነት የገጠመች፣ በመሆኑም ከብዙ አገሮች በተለይም ከጎረቤቶችዋ ጋር የተበላሸ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ያላት አገር፣ በድህነት ተርታ በስተመጨረሻ ከተሰለፉት አገራት የተሰለፈች፣ በፐርካፒታል መስፈርት ከአፍሪካ ቀዳሚ ስደተኞች የምትልክ አገር፣ ዜጎችዋ የበረሃና የውሃ ሲሳይ የሆኑባት እንደዚሁም  የዜጎችዋ አካላት እየተበለተ የሚቸበቸብባት አገር ሆነች፡
፡

ያቺ ጥሩ የወደፊት ተስፋ የነበራት ኤርትራ ለዚህ ሁኔታ እንዴት ልትዳረግ ቻለች የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ ለዚህ ጥያቄ በርካታ መላምቶች ማስቀመጥ የሚቻል ቢሆንም እስከ ኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ማብቂያ ድረስ በኤርትራ ከፍተኛ ባለስልጣን የነበሩ፤ G-15 በመባል ከሚታወቁትና የሪፎርም ጥያቄ ካስነሱት የሻእቢያ ባለስልጣናት መካከል አንዱ የሆኑት ሃይለ መንቀርዮስ ያስቀመጡትን መመልከት ጥያቄውን ለመመለስ በቂ ስእል ይሰጣል የሚል እምነት አለኝ፡፡ (በኤርትራ የመንግስት አወቃቀር ማሻሻያ ያስፈልጋል በሚል የተቃውሞ ቡድን ከፈጠሩት 15 ባለስልጣናት መካከል 12ቱ ኤርትራ ውስጥ ለእስር የተዳረጉ ሲሆኑ ሃይለ መንቀርዮስን ጨምሮ አምባሳደር አድሐኖም እና መስፍን ሐጎስ) በስራ ምክንያት ውጭ አገር ስነለበሩ ከእስር አምልጠዋል፡፡

ሃይለ መንቀርዮስ ከዚህ በታች የሰፈረው አስተያየት የሰጡት በሐምሌ ወር 2004 ዓ.ም በደብረዘይት በተካሄደው የኤርትራ ወጣቶች ኮንፈረንስ ወቅት ወጣቶቹ ያቋቋሙትን ማህበር ለመምራት ከተመረጡት አስተባባሪዎች ጋር በአዲስ አበባ ባደረጉት ውይይት ወቅት ነበር፡፡ (ስለወጣቶቹ ኮንፈረንስ በሚቀጥለው ጽሑፌ እመለስበታለሁ፡፡)

**እንደ ሃይለ መንቀርዮስ እምነት ኤርትራ ውስጥ ለተፈጠረው ቀውስ ዋናው መንስኤ ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ የአሁኑ ህግደፍ ‹የነጻነት ጥያቄ አንግቦ ሲታገልለት የነበረው አስተሳሰብ መንግስት ከመሰረተ በኃላም መቀየር ባለመቻሉ እና በበረሃ ይጠቀምበት የነበረው አሰራር አስመራ ከገባ በኃላም ይዞት በመቀጠሉ ነው፡፡›**

ይህ አስተሳሰብ ህግደፍን ከውስጥና ከውጭ አብጠርጥሮ ከሚያውቅ ባለስልጣን መቅረቡ አሁን ኤርትራን ወደማትወጣው ቀውስ የከተተው ሃይል አቋም፤ታሪክና እምነት ምን ይመስል እንደነበረና ምን እንደሆነ በግልጽ ሚያሳይ ተጨባጭ ምስክር ነው፡፡

በኤርትራ የነጻነት ትግል ታሪክ የመጀመርያው ትልቁ ሃይል የኤርትራ ነጻነት ግንባር ( ELF) ወይም ጀብሃ ነበር፡፡ ይህ ግንባር ከኤርትራ ህዝብ የነጻነት ግንባር (EPLF) ወይም ሻዕቢያ በፊት የነበረና በሰው ሃይልም በመሳርያም የደረጀ ግንባር እንደነበረም የታሪክ መዛግብት አስፍረውታል፡፡ ጀብሃ ከሻዕቢያ ጋር ሲነጻጸር ለዘብተኛና አለመግባባቶችን በድርድር ለመፍታት የሚሞክር ሃይል የነበረ ሲሆን በአንጻሩ ሻዕቢያ ግትርና ሁሌም በጉልበት የሚያምን ነበር፡፡ በዚህ ባህርዩም የበለጠ ሃይል የነበረው ጀብሃን ከጨዋታ ውጪ አደረገው፡፡

በራሱ በሻዕቢያ ፓርቲ ውስጥም በተለይ ለፕሬዚዳንት ኢሳያስ ተቀናቃኝ መስሎ የታያቸው አካል ከማስወገድ የቦዘኑበት ጊዜ የለም፡፡ የለሊት ወፍ (መንካዕ) የሚል ቅጥያ ተሰጥቶት ተቀናቃኞችን የተወገዱበት ወቅት አንዱ ክስተት ነበር፡፡

እነዚህ የለሊት ወፍ የሚል ቅጥያ የተሰጣቸው ታጋዮች የኤርትራ የነጻነት ጥያቄ አንግበው ሲታገሉ የነበሩ፤ ፕሬዚዳንት ኢሳያስን ጨምሮ በወቅቱ ከነበሩ ታጋዮች በትምህርታቸው እና በአስተሳሰባቸው የላቁ ወጣቶች እንደነበሩ በሻእቢያ ትጥቅ ትግል ያለፉ ምሁራን ያረጋግጣሉ፡፡ ታድያ እነዚህ ወጣቶች የስልጣን ተጠያቂነት (Democratic Accountability) ይኑር ብለው ጥያቄ በማንሳታቸው ግራ ዘመም በመሆናቸው የትግላችን አደጋዎች ናቸው በሚል ምክንያት ልክ የደርግ ኮሚቴ ከ60 በላይ የአጼ ኃ/ስላሴ ባለስልጣናት ወደ ፍርድ ሳይቀርቡ እንደፈጃቸው ፕሬዚዳንት ኢሳያስም ከእርሳቸው የሚልቁትን እና ለስልጣናቸው ተቀናቃኝ የሆኑትን ወጣቶች እርምጃ እንዲወሰድባቸው አደረጉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ከለሊት ወፍ ጭፍጨፋ በኃላ እንደዚሁ በአረብኛው ‹የሚን› (ቀኝ ዘመም) የሚል ቅጥያ የተሰጠው የፕሬዚዳንት ኢሳያስ ተቀናቃኞች የተወገዱበት ወቅት ሌላው ክስተት ነው፡፡ ቀኝ ዘመም ናቸው በሚል የተወገዱት ወጣቶች ስልጣን በሙሉ ወደ አንድ ሰው እየተሰበሰበ ነው፤ ተጠያቂነት መኖር አለበት የሚል ጥያቄ በማስነሳታቸው ነበር፡፡ ኢሳያስ ተቀናቃኞቻቸውን ለማስወገድ ይረዳቸው ዘንድም ከዋናው ግንባር መዋቅር ውጪ በራሳቸው የሚመራ እንደ ‹ሐለዋ ሳውራ› (ጥበቃ) የመሰሉ ተጓዳኝ መዋቅሮች ማቋቋም አንዱ ስልታቸው ነበር፡፡

ሻእቢያ በትጥቅ ትግል ወቅት ግንባሩ የሚመራበት ቻርተር ነበረው፡፡ በዚሁ ቻርተር መሰረት ድርጅቱን የሚመሩ አመራሮች ይመረጣሉ የአመራሮቹ የሥራ ዘመንም ለ3 ዓመታት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ይህ ማለት የድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ በየ3 ዓመቱ ይካሄዳል ማለት ነው፡፡ በዚሁ ቻርተር መሰረት ግንባሩ የመጀመርያ ጉባኤ ያደረገው እ.ኤ.አ በ1977 ነበር፡፡ በዚህ ጉባኤ ሮመዳን መሐመድ ኑር የተባለ ታጋይ ዋና ጸሐፊ በመሆን ሲመረጥ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ደግሞ ምክትል ሆነው ተመረጡ፡፡ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከሻእቢያ ጋር የጠበቀ ግንኙነት የነበራቸው ምንጮች እንደሚያረጋግጡት ሮመዳን መሐመድ ኑር የግንባሩ ዋና ጸሐፊ ሆኖ ይመረጥ እንጂ የፖለቲካና የወታደራዊ አመራርን ጨምሮ ግንባሩን በዋናነት ሲመሩ የነበሩ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ናቸው፡፡

ታድያ በግንባሩ ቻርተር መሰረት በየሦሥት ዓመቱ መካሄድ የነበረበት ጠቅላላ ጉባኤ ለአስር አመታት ሳይካሄድ ቆይቶ ሁለተኛው ጉባኤ የተደረገው እ.ኤ.አ በ1987 ነበር፡፡ ለምን በቻርተሩ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤ በሦሥት አመት አልተካሄደም የሚል ጥያቄ ሲነሳ ወደ በረሃ የወጡት ለጦርነት ሳይሆን ለሌላ ጉዳይ ይመስል በወቅቱ ምክትል የነበሩት ኢሳያስ ‹ጦርነት ውስጥ ሆነን ጉባኤ ማካሄድ አንችልም የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት፡፡› አስር አመት ሙሉ ግንባሩን ለመቆጣጠር የሚያስችላቸው ሴራ ሲያሴሩ ነበር የከረሙት፡፡ የሚገርመው ግን አሁንም ድረስ ህገ መንግስት ለምን አይጸድቅም፣ ምርጫ ለምን አይካሄድም የሚል ጥያቄ ሲቀርብላቸው ‹ከኢትዮጵያ ጋር በጦርነት ውስጥ ስለምንገኝ፣ ኢትዮጵያ መሬታችን ስለወሰደች ሁኔታዎች አልተመቻቹልምን› የሚል ምላሽ መስጠታቸው ነው፡፡ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ የሚባለው እንዲህ የመሰለውን ነው፡፡

አቶ ሃይለ መንቆርዮስ እንዳሉት ህግደፍ አስመራ ከገባም በኃላ በሽምቅ ውጊያ የነበረው አሰራር የሲቪል መንግስት እንዲመራበት ተደረገ፡፡ ከባለ ስልጣኑ አባባል በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለው ወታደር /ጦርነት የሚመራበት ህግ ሲቪል/የአገር ግንባታ እንዲመራበት ተደረገ ማለት ነው፡፡ በጫካው ህግ መሰረት ጉልበትና መሳርያ ዋና መመሪያዎች ናቸው፡፡ ይህንኑ አሰራር ለውጥ ሳይደረግበት ወደ ከተማ ከገባ አገሪቱና ህዝቡ የሚመሩት በተቋም ሳይሆን በአንድ ካቦ እና ይህ ካቦ በሚያሰማራቸው ነፍሰ ገዳዮች አማካኝነት ይሆናል ማለት ነው፡፡ በኤርትራ የተከሰተው ያለምንም ማጋነን ይህንኑ ነው፡፡

በጦርነት ወቅት ነጻ ፕሬስ ሚባል ታሪክ እንደማይኖር የታወቀ ነው፡፡ በጦርነት ወቅት ከፍተኛው ስልጣን በወታደራዊ መሪው ላይ እንደሆነም ይታወቃል፡፡ ወታደራዊ መሪው የሚመረጠውም ሰራዊት ተሰብስቦ በድምጽ መስጫ ሳጥን በማድመጥ ሳይሆን በወታደራዊው አሰራር መሰረት ነው፡፡ በወታደር ቤት ነጻ ገበያ ብሎ ነገርም የለም፡፡ ግዢ የሚፈጸመው በማእከል፣ ክፍፍል የሚደረገው በማእከል፣ ሽያጭ ካለም የሚከናወነው በማእከል፣ መመሪያም ሆነ ስትራቴጂ ወዘተ የሚመነጨው ከማእከል ነው፡፡ ሌላም ሌላም………..

የሽምቅ ውጊያው አሰራርና ባህርይ እንደወረደ ለሲቪላዊ መንግስት መመሪያነት ስለዋለም በአገሪቱ ከአንድ ፓርቲ በላይ እንዳይኖር ፣ ለለውጥና ማሻሻያ የሚያቀነቅን ማንኛውም ሃይል እንዲመታ፣ ነጻ ፕሬስ እንዲዘጋ፣አገሪቱ ህገ መንግስትና የህዝብ ውክልና ያለው ተመራጭ ሳይኖራት በአንድ ፓርቲ እና አንድ

ግለሰብ እንድትመራ ተደርጓል፡፡ ለዚህም ይመስላል አንጻ̈ ኤርትራዊት ‹ **ከሳሕል ወደ አስመራ የገባው ሻዕቢያ ሳይሆን ወደ ሳሕል የገባችው አስመራ ነች** › ያለችው፡፡

አቶ ሃይለ ሻእቢያ የሚመራበት ስርአት ሲገልጹ ኢትዮጵያን ጨምሮ እንደ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ‹ዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት› መሆኑን ያስቀምጣሉ፡፡ ልዩነት ካለው ይላሉ አቶ ሃይለ፤ ልዩነት ካለው እንደ ኢትዮጵያ የመሰሉ አገሮች ቁጥጥሩን ‹ትንሽ› ላላ ሲያደርጉት ሻእቢያ ደግሞ ‹ትንሽ› ጠበቅ ስላደረገው ነው፡፡ ለዚህም ተጠያቂው ስርአቱ ሳይሆን ኢሳያስ አፈወርቂ መሆናቸውን በአጽንኦት ይሞግታሉ፡፡

አቶ ሃይለ መንቆርዮስ በኤርትራ ስለተከሰተው ችግር የበረሃ አሰራር አለመለወጡ መሆኑን ቢገልጹም የችግሮች ሁሉ ቁንጮ አድርገው የሚያሥቀምጡትና እንደ ዋነኛ ተጠያቂ የሚያቀርቡት በአንድ ወቅት እርሳቸውም ሲመሩበት የነበረው ሥርዓትን ሳይሆን ኢሳያስ አፈወርቂ እንደሆኑ ያሰምሩበታል፡፡

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ‹የኤርትራን ችግር ለመቅረፍ የሰው ወይስ የስርአት ለውጥ› የሚለውን ጥያቄ መነሳት ያለበት፡፡ ለተለያዩ ዓላማዎች የሚመሰረት ስርአት መነሻው ምን ይሁን ምን ከተመሰረተ በኃላ ስርአቱን ለመምራት የሚቀመጥ መሪ የሥርአቱን ዋና ዓላማ ለማሳካትና ስርአቱን እንደ ስርአት ለማስቀጠል ነው፡፡ ከዚህ የተለየ ዓላማ ያለው ግለሰብ ስርአቱን አፍርሶ በሌላ መተካት አለበት ወይም ደግሞ ሌላ ተቀናቃኝ ስርአት መመስረት መቻል አለበት፡፡

አገራችን ለዘመናት ስትመራበት የነበረችው የፊውዳል ስርአት ነገስታቱና ንጉሰ ነገስታቱ ቢለዋወጡም መሰረታዊ የሆኑት የስርአቱ መርሆዎች (ስልጣን ከፈጣሪ የተሰጠ እንደሆነና ለአንድ ቤተሰብ ብቻ የተወሰነ መሆኑ፤ አገሪቱም ህዝቦችዋም የንጉሰ ነገስቱ መሆናቸው…ወዘተ) ሳይሸራረፉ ጸንተው ቆይተዋል፡፡

ስልጣን የህዝብ መሆኑን፤ አገር በውስጥዋ የሚኖሩ ህዝቦች ሃብት እንጂ የአንድ ንጉሰ ነገስት አለመሆንዋን እንደዚሁም በአንድ አገር የሚኖሩ ህዝቦች መብት የሚወሰነው በንጉሰ ነገስቱ መልካም ስጦታ ሳይሆን ህዝቦች የራሳቸውን መብት የሚወስኑት በራሳቸው መሆኑን ለማረጋገጥ እነዚህን አስተሳሰቦች የሚቃወመው ወይም የማይቀበለው ዋናው የሥርአቱ አስተሳሰብ ካልተሰበረ/ካልተወገደ በስተቀር አጼ ዮሐንስ በአጼ ምንሊክ ስለተተኩ ወይም አጼ ምንሊክ በአጼ ኃ/ስላሴ ስለተተኩ የስርአቱ አንኳ̈ር አስተሳሰቦች ሊለወጡ አይችሉም፡፡

የደርግ ስርአትም የወሰድን እንደሆነ ሁሉንም አለመግባባት በጉልበት ብቻ ለመፍታት መሞከር፤ ከአንድ ፓርቲ ውጪ ሌላ ተቃዋሚ እንዳይኖር ማድረግ፤ነጻ ፕሬስ እና መሰረታዊ የዴሞክራሲ ጥያቄዎች

ለማስተናገድ ዝግጁ አለመሆን ወዘተ የወታደራዊ አስተሳሰብ ይዞ ስርአቱን ለመቀጠል የተሰለፈ ሃይል እስካለ ድረስ መንግስቱ ኃ/ማርያም ቢለቅ፣ ወይም ፍስሃ ደስታ ቢተካ ወይም ተስፋየ ወ/ስለሴ ቢሾም የአገሬ ሰው እንደሚለው ‹ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም› ስለሆነ የሰዎች መለዋወጥ መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም፡፡ እነዚህ አስተሳሰቦች ለመምታት የግድ ስርአቱ መመታት መቻል አለበት፡፡

የናዚ አስተሳሰብና አመራር ሊከስም የቻለው ሂትለር በመሞቱ አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህንን አስተሳሰብ ሊሰብር የሚችል ሌላ ተራማጅ አስተሳሰብ በመምጣቱና የጸረ ናዚ አስተሳሰብ ልዕልና ሊይዝ በመቻሉ ነው፡፡ ሶሻሊዝም/ኮምዩኒዝም ሊከስም የቻለው ሌኒን ስለሞተ ወይም ሚካኤል ጎርቫቸው ስለሰነፉ አይመስለኝም፡፡ ይልቁንም የሊበራሊዝም ወይም የነጻ ገበያ አስተሳሰብ በተሻለ መልኩ ሊያሰራ እንደሚችል በአስተሳሰብና በተግባር ስላስመሰከረ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ታድያ ኤርትራ አሁን ለምትገኝበት አስከፊ ሁኔታ ሃይለ መንቆርዮስ እንዳሉት የበረሃው ስርአት በከተማም እንዲሰፍን በመደረጉ ነው በሚለው እሳቤ ስምምነት ሊኖር የሚችል ቢሆንም ዋናው ተጠያቂ ህግደፍ ሚከተለው ስርአት ሳይሆን ስልጣኑን በብቸኝነት ተቆናጥጠው የሚገኙት ኢሳያስ ናቸው የሚለው ድምዳሜያቸው ግን መልሰው መላልሰው ሊያጤኑት የሚባ ጉዳይ ነው የሚሆነው፡፡

ይህ ጥገናዊ አስተሳሰብ (ህግደፍን/ሻእቢያን እንደ ስርአት መናድ ወይም የሚከተለውን አስተሳሰብ ወሳኝ በሆነ መልኩ መቀየር ሳይሆን ኢሳያስን ከስልጣን በማውረድ ሌላ ሰው ስልጣን እንዲይዝ ማድረግ) የአቶ ሃይለ ብቻ ሳይሆን የሻእቢያ ታጋይ ነበር አባላት ሁሉም ለማለት ይቻላል አጥብቀው የያዙት አስተሳሰብ ነው፡፡

ለዚህም ይመስላል በስልጣን ላይ ያለው ስርአት ኤርትራን እንደ አገር ወደ እስርቤትነት የቀየረ፣ ስፍር ቁጥር የሌለው ወጣት ቀየውን እየጣለ ለስደት፣ ለሞትና ለአካል መጉደል የዳረገ ባጠቃላይ የለየለት አምባገነናዊ መንግስት ለሆነው ህግደፍ በግላጭ ከማውገዝ እና እድሜውን ሚያጥርበት መንገድ ከመቀየስ ይልቅ በኤርትራ ውስጥ ለተፈጠረው እና እየተፈጠረ ላለው መጠነ ሰፊ ውድመት መነሻውና መድረሻው ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አድርገው የሚቆጥሩት፡፡ ከሰውየው (ኢሳያስ) ጋር እንጂ ኤርትራን እያቆረቆዘ ካለው ስርአት እና ምናልባትም ኢሳያስ አሁን ለያዙት ባህርይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረገው አስተሳሰብና አካሄድ እንዲስተካከል ወይም እንዲፈርስ የሚያደርጉት ትግል ቀጫጫ የሆነው፡፡

ስለሆነም የኤርትራ መጠነ ሰፊ ችግር ሊቃለል የሚችለው እና የወደፊትዋ ኤርትራ ለዜጎችዋ ምቹ መኖርያ እንድትሆን ለማድረግ የትግል አቅጣጫው ግለሰብን ከስልጣን ማውረድ ሳይሆን ግለሰቦችን እና የግለሰቦችን ባህርይ ሊፈጥርና ሊቀይር የሚችል ስርአት እና አስተሳሰብ ማስተካከል ላይ ቢሆን አሁን ከምናውቃት ኤርትራ በእጅጉ የተለየች፣ ከጎረቤቶችዋ እና ከአለም ማህበረሰብ ጋር ተግባብታና ተከባብራ የምትኖር፣ የዜጎችዋ እስር ቤት ሳትሆን ምቹ መኖርያ የሆነች ኤርትራ ማየት እምብዛም ከባድ አይሆንም፡፡

*ለአስተያየትዎ፡- jhoniabraha@gmail.com*